# ልጅ ተክሌ ምነው ጥምረትን ጠመዱ - ውህደትን ወደዱ?

ከጥቂት ቀናት በፊት ልጅ ተክሌ ከካናዳ "***ያጣነው ጥምረት አይደለም፡ ድፍረት ነው፡***" በሚል ርዕስ፡- የአፋር ሕዝብ ፓርቲ፣ ግንቦት7 ና የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነትና የፍትህ ንቅናቄ ጥምረት መመስረታቸውን አስመልክተው ያቀረቡልንን ጽሁፍ ያነበብኩት በጥሞና ነው።በርካታ ነጥቦችን የዳሰሰ ማለፊያ ጽሁፍ ነው።

የልጅ ተክሌን ጽሁፍ ሳነብ፤ አንዳንዴ ቁጭትና ምሬታቸው የኔም ቁጭትና ምሬት እየሆነ አብሬያቸው ስመረርና ስቆጭ፤ አንዳንዴ ደግሞ፡- ውህደት እንዴት? ውህደት ማ ና ማ? የሚሉትን ጥያቄዎች ችላ ብለው በደፈናው መጣመር ሳይሆን "መዋሃድ" ነው መፍትሄው በማለት የሚሰነዝሩት ሃሳብ የቀጭን ጌታ ቀጭን ትዕዛዝ እስኪመስለኝ በአግራሞት እየቆዘምኩ፤ አልፎ አልፎ ደግሞ፡- ፋታ ወሰድ አድርጌ በምሬቶቻቸውና በምኞቶቻቸው መካከል ያሉትን ተጨባጭና ነባራዊ ዕውነታዎች እያብሰለሰልኩ ነበር የልጅ ተክሌን ጽሁፍ የዘለቅኩት። ማብሰልሰሌም ይህችን የዛሬዋን ጽሁፍ ወለደ።

ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት ልጅ ተክሌ በጽሁፋቸው፤ ጥምረት፤ህብረት፤ግንባር፤ቅንጅት፤መድረክ....አይነቶቹ የትብብር እርከኖች ችግር ፈጣሪ እንጂ መፍትሄ ቀማሪ አይሆኑም የሚል ጠንካራ ዕምነት እንዳላቸው በተደጋጋሚ ገልጸዋል። "እባብ ያየ በልጥ በረየ" እንዲሉ፡-ልጅ ተክሌ፡- ጥምረት፤ ግንባር፤ህብረት...በመሳሰሉት የትብብር አይነቶች ላይ የሚያሰሙት ምሬት የመነጨው ጥቂት ለማይባሉ ዘመናት በተደጋጋሚ ካስተናገድናቸው ውድቀቶች መሆኑን ከጽሁፋቸው እንድንረዳ አድርገዋል።

ይህ ምሬታቸው የብዝዎቻችንም ምሬት ይመስለኛል። እኔም ቀደም ባለ አንድ ጽሁፌ፤ ህብረት ሲሉን ህብረት ስንል፤ቅንጅት ሲሉን ቅንጅት ስንል፤ ....በሚል ምሬትም ባይሆን መሰላቼቴን መግለጼን አስታውሳለሁ።ልጅ ተክሌም ያሉን ይህንኑ ነው።

ልጅ ተክሌ ከላይ የተዘረዘሩት የትብብር አይነቶች ውድቀት እንጂ መፍትሄ አያመጡም ! ለሚለው አመለካከታቸው እንደ ምክንያት ያስቀመጧቸው ነጥቦች፡-

- ✏ ሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት መመስረትና ማምጣት ወያኔን ከመጣልና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ከመመስረት ጋር ምንም አያገናኘውም።
- ✏ ጥምረትና ህብረትን የምጠላባቸው ምክንያቶች፡ አጉል ፉክክር ይፈጥራሉ
- ✏ ሕብረት የመፍጠር ትግል እንደ ግብ
- ✏ ወያኔ አንዱን የጥምረት አባል ድርጅት አባብሎ መፈረካከስ ሊፈጠር ይችላል፡

ከብዙ በጥቂቱ የልጅ ተክሌ ምሬት ምክንያቶች ከላይ የተዘረዘሩት ይመስሉኛል።ስኬት ካልታደለው የትግል ታሪክ ከተነሳን ልጅ ተክሌ ምንም ስህተት የለባቸውም። ነገም በወያኔ አባባይነት መፈረካከስን የሚፈጥሩ አየለ ጫሚሶዎች እንደማይኖሩ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ነገም እንደ ልደቱ ኢዴፓና እንደ ኃይሉ ሻውል መ ኢ አ ድ በውህደት ማግስት በውህደቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ በሚኖራቸው የወንበርና የስልጣን እርከን እንደማይጣሉ ታቦት ይዘን ልናስምላቸው አንችልም።

ሕብረት የመፍጠር ትግል እንደ ግብ እየታየ ነው የሚባለውም ዕውነት አለው።ስለ ሕብረት ሲወራ 20 ዓመታት ተቆጠሩ። ይወራል፤ ይመሰረታል ይጨነግፋል፡፤ከትናቱ ስህተት ተምረን በሚል ፈሊጥ ታጅለን ነገም ሌላ ሕብረት መመስረትን ግብ አድርገን እንነሳለን። የፈነዳ ጎማ እያደስን ዋናውን ጉዞ ሳንጀምር ሁለት አስርት አመታት ተቆጠሩ።አዎ ህብረት መመስረት ዘላለማዊ ግባችን ሆነ። ልጅ ተክሌ ያሉት አንጀቴ ጠብ ነው ያለቺው።

ለኔ ትንሽ አልዋጥ ያለኝ ፡- <u>ሰፊና ሁሉን አቀፍ ህብረት መመስረትና ማምጣት ወያኔን ከመጣልና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ከመመስረት ጋር ምንም አያገናኘውም።</u> የሚለው አመለካከታቸው ነው። የጥምረት፤የህብረት፤የመድረክ፤.....አይነት ትብብሮች ውጤት አያስገኙም ብሎ ማመን አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ሰፊና አገር አቀፍ ህብረት መመስረት ወያኔ ከመጣል ጋር ግንኙነት የለውም ማለት ግን ፍጹም መቆሚያና መመርኮዣ የሌለው አመለካከት ይመስለኛል።

ልጅ ተክሌ ይህ ሲሉ፡ በምሬቶቻቸውና በምኞቶቻቸው መካከል ያሉትን ተጨባጭና ነባራዊ ዕውነታዎች ለማጤን ግዜ ያጠፉ አይመስለኝም።ምሬቶቻቸው ከላይ የተዘረዘሩት የትብብር አይነቶች ወጥነት ያለው ሥራ ለመስራት አያስችሉም። ጭራሹኑ ከድርጅት ስሜት ካለመለቀቅ በሚመነጭ እኔ እበልጥ ፤ እኔ እበልጥ ፉክክር ለውድቀት ይዳርጋሉ በሚል እምነት ላይ ያጠነጠኑ ናቸው።ነባራዊ ሃቁም የሚያሳየው ይህንኑ ነውና እንስማማለን።

በሌላ በኩል የልጅ ተክሌ ምኞት ደግሞ **ውህደት** እንዲፈጠር ነው! ውህደት ማለት ለኔ እስከሚገባኝ ፍጹም የሆነ አንድነት፤ ማለት ነው። ሊለያዩ የማይችሉ ውህዶች ። ተጨባጩ የተቃዋሚው ጎራ አሰላለፍ፤አደረጃጀትና የትግል መርህ ደግሞ ይህን የሚያመለክት አይደለም። ጎሳን ያማከለ አደረጃጀት ያላቸውም ህብረ-ብሄር ድርጅቶችም በተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈዋል።

እንግዲህ በምኞት ደረጃ እነኚህ የሰማይና የምድር ያህል የመርህና የአላማ ልዩነት ያላቸው ድርጅቶች በተዓምር ቢዋሃዱ እኔም ልጅ ተክሌም ሌላውም ይመኛል። ችግሩ  ግን እንዴት ሊዋሃዱ ይችላሉ? ከሚለው ጥያቄ የሚወልድ ነው። ያለ ማዕዘን አየር ላይ ከሚንሳፈፍ ምኞት ርቀን መሬት ላይ ያለውን ዕውነት ስንመለከት የምናገኘውም ይህንኑ ነው። ውህደት የማይቻል ባይሆንም ብዙ ሥራና ግዜ ይጠይቃል። ልጅ ተክሌ ደግሞ ጀንበር ሳታዘቀዝቅ  ዛሬውኑ ተዋሃዱ ነው የሚሉት። "ባምር ጠላሁ እንዳለቺው ...." ቢሆንማ መች ከፍቶን።

ልጅ ተክሌ፡ በምሬቶቻቸውና በምኞቶቻቸው መካከል ያሉትን ተጨባጭና ነባራዊ ዕውነታዎች ለማጤን ግዜ ያጠፉ አይመስለኝም ያልኩትም ከዚህ በመነሳት ነው።ልጅ ተክሌ በተለይ በምሬት የሚዘረዝሯቸው በርካታ ዕውነቶች አሏቸው፡፤ ይሁንና እንደመፍትሄ በሚያስቀምጡት ሃሳብ ላይ ግን ቅራኔዎች ይስተዋላሉ፡፤

በአንድ በኩል ተዋሃዱ ይላሉ፤ በሌላው በኩል አገር አቀፍ ህብረት መፍጠር ወያኔን ታግሎ ከመጣል ጋር ግንኙነት የለውም ይላሉ። ለኔ እስከገባኝ የሃገር አቀፍ ህብረት ምስረታ አስፈላጊነት ጎልቶ የወጣው በነፍስ ወከፍና በነጠላ ወያኔን ለመጣል የተደረገው ሁሉ ሙከራ ውጤት ሊያስገኝ ባለመቻሉ ነው። ስለዚህ አገር አቀፍ ህብረት ምስረታው ወያኔን ከመጣል ጋር በአንድ ብቻ ሳይሆን በአራቱም ማዕዘናት ግንኙነት አለው፡፤

በርግጥ ውህደት ከየትኛውም የትብብር እርከን በተሻለ ለውጤት የሚያበቃ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፤ በዛው መጠንም በአንድ ጀንበር ተቀልሶ ዘው ተብሎ የሚገባበትም ደሳሳ ዛኒጋባም አይደለም። ከብዙ ስራ በኋላ የሚመጣ እንጂ። ስለዚህ ማሰብ ያለብን ወደ ውህደት የሚያደርሰውን ጎዳን እንዴት እናቀላጥፈው? ከውህደት በፊት ያሉት የትብብር እርከኖች(ጥምረት፤ቅንጅት፤ግንባር...) እንደ ከዚህ በፊቱ ለውድቀት ሳይዳርጉን እንዴት ልንጓዝባቸው እንችላለን? ስለሚሉት ጥያቄዎች እንጂ ጭራሹኑ አያስፈልጉም ብሎ መደምደም ከጭብጡ መራቅ ይሆናል።

ከዚህ በመነሳት የልጅ ተክሌን ጽሁፍ ያየሁት ችግርና ስጋቶችን ከትናንት ልምድ በማጣቀስ ረገድ ጠንካራ ጎን ያለው መሆኑን ሲሆን፡-መፍትሄ በማመላከት ረገድ ግን መሬት ያላረፈ ተንሳፋፊ ሃሳቦችን መያዙን ነው።

ልጅ ተክሌ በጽሁፋቸው፡- ግንቦት ሰባት ድርጅት በሴፕቴመበር 3 ርእሰ አንቀጹ እንዳለው ይሄ ጥምረት **"የተደራዳሪዎችን ቁጥር ከመቀነስ ውጪ" ምንም አይነት የላቀ ሚናና ፋይዳ አይኖረውም።** ብሏል ሲሉ አስፍረዋል። በግንቦት7 ርዕሠ አንቀጽ ላይ ግን ልጅ ተክሌ የጠቀሱትን ሃሳብ የሚያንጸባርቅ ሃረግ አላገኘሁም። የግንቦት7 ርዕሰ አንቀጽ የሚለው "**ጥምረቱን የፈጠርን ድርጅቶች ከአሁን በኋላ እንደ አንድ ድርጅት ሆነን የምንደራደር በመሆኑ በመጠኑም ቢሆን የተደራዳሪዎችን ቁጥር በመቀነስ ረገድ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብለን እናምናለን።**"ነው።

ልጅ ተክሌ በግንቦት7 ርዕሰ አንቀጽ ውስጥ ያልተባለ ነገር ለምን ተባለ አሉ? ብሎ መጠየቅ አግባብ ነው። እኔ እንደሚመስለኝ ግን ልጅ ተክሌ አሁንም የነገሩን እንዲሆን የሚመኙትን እንጂ ግንቦት7 በገሃድ ያስቀመጠውን ጭብጥ አይደለም።

ልጅ ተክሌ ሊነግሩን የፈለጉት ግንቦት7 ራሱ በጥምረቱ አስፈላጊነት እምነት እንደሌለው በርዕሰ አንቀጹ መግለጹን ነው ። ወረድ ብለው ደግሞ ግንቦት7ቶች የሚሰሩትን ያውቃሉ ይላሉ። ታዲያ አስፈላጊነቱን የማያምንበትን ጥምረት የሚመሰርት ድርጅት እንዴት የሚሰራውን ያውቃል ሊባል ይችላል? ገሎ ማዳን አይሆንም...!?

ከውህደት በተጓዳኝ እንደመፍትሄ የተጠቀሰው ሌላው የልጅ ተክሌ ሃሳብ ደግሞ፤ ሁሉም በነፍስ ወከፍ ስራውን ይስራና ውህደቱ በራሱ ግዜ ይመጣል የሚል ነው። ሁሉም ግዜውን ጠብቆ በ(Evolution)  ይመጣል የሚል ይመስላል። እንደ  እኔ እምነት ግን ወደ ውህደት የሚያመራ ጎዳና ላይ ቆመው አንድ ብለው እርምጃ ካልጀመሩ በራሱ ግዜ አንሳፎ ውህደት አምባ የሚጥል ተዓምር የለም። ለዚህም ነው ከውህደት በፊት ያሉ የትብብር እርከኖች ብንጠላቸውም የግድ ናቸው የምለው።

ዛሬ በግንቦት7ና በሌሎች 2 ድርጅቶች የተመሰረተው ጥምረት ችግር ሊገጥመው አይችልም የሚል እምነት የለኝም። ሊገጥመው ይችላል። ዋናው መታወቅ ያለበት ግን ጥምረት ማለት በተለይ alliance የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ፍቺ እንደሚያመለክተው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች/አካሎች በተወሰነ ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸው ወይም የሚያደርጉት የትብብር ስምምነት ማለት በመሆኑ ጥምረት የመሰረቱትም ድርጅቶች የሚኖራቸው ትብብር በውስን ጉዳዮችና አላማዎች ላይ ብቻ እንደሆነ ነው።

ግንቦት7 በፕሮግራሙ ያስቀመጠው ግብ፡- ወያኔን አስወግዶ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ነው፡፤ ኪዚህ በኋላ በፖለቲካው ውስጥ ስለሚኖረው ሚና ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም። ስለዚህም ግንቦት7 ከማንም ወይም ከየትኛውም ድርጅት ጋር ትብብር መሰረተ

የሚባል ዜና ስንሰማ ወዲያውኑ ግልጽ ሊሆንልን የሚገባው፡-ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ለመተባበር እንደተስማማ ነው።ከዚህ ውጭ በግብርና ፖሊሲ፤ በኢኮኖሚ ፖሊሲ፤ ወይም በመሳሰሉት .... ጉዳዮች የሚያደርገው የስምምነትም ሆነ የትብብር እንቅስቃሴ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ነው።

ለዚህ ውስን፤ ወያኔን የማስወገድ ዓላማ ደግሞ አገር አቀፍ ህብረት መመስረት እጅግ በጣም ጠቃሚ መሆኑ ለማንም ይጠፋዋል አልልም። ከግንቦት7 ርዕሰ አንቀጽ የተረዳሁትም ይህንኑ ነው።በርግጥ እኔም ብሆን በግንቦት7 ርዕሠ አንቀጽ ላይ አንዳንድ ጥያቄ የፈጠሩብኝ ጉዳዮች አልጠፉም። በተለይ **ጥምረታችንን አጠናክረን ወደ ውህደት ልናመራ የምንችልባቸውን መንገዶች ለመቀየስም ወስነናል። ውህደት እስኪፈጠር ድረስም በአንድ ድምጽ እንናገራለን፤ ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ ኃይሎቻችንን እናቀናጃለን።** የሚለው ክፍል ግራ አጋብቶኛል።

ግንቦት7 ከጎሳ ድርጅቶች ጋር ወደ ውህደት የሚያመራው እንዴት ነው? ውህደት ሁለንተናዊ አንድነት ማለት ነውና፤ የጎሳ ድርጅቶችና ህብረ-ብሄር ድርጅቶች የሚዋሃዱበት ዘዴ ግልጽ አልሆነልኝም። ይህን በተመለከተ ግንቦት7 ተጨማሪ ማብራሪያ እንደሚያክል ተስፋ አለኝ።

በመጨረሻም ሰፊ ሃሳባቸውን ለንባብ አቅርበው እኔንም እንደአቅሜ እሞጫጭር ዘንድ ምክንያት ለሆኑኝ ለጸሃፊ ልጅ ተክሌ ምስጋና እያቀረብኩ፤ የዛሬውን ጽሁፌን በዚሁ እቋጫለሁ።

አዜብ ጌታቸው

azebgeta@gmail.com